# በውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ዘርፍ ለሥራ የሚሰማሩ ዜጎችን ለማብቃት የተዘጋጀ የአሰልጣኞች ስልጠና ሰነድ

የካቲት 2015
አዲስ አበባ

# ፍልሰትን በተመለከተ ዘላቂ መፍትሄዎች ለማምጣት የሚደረግ ትብብርና አጋርነት

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አለም አቀፍ የፍልሰት ድርጅት እና የኢትዮጵያ በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት አገናኝ ኤጀንሲዎች አሠሪ ፌዴሬሽን ትብብር የታተመ

Cooperation on Migration and Partnerships to Achieve Sustainable Solutions (COMPASS)

IOM UN MIGRATION | ETHIOPIA
COMPASS Guiding safe migration
EOEAF

## በውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ዘርፍ ለሥራ የሚሰማሩ ዜጎችን ለማብቃት የተዘጋጀ የአሰልጣኞች ስልጠና ሰነድ


መግቢያ ..... 1

**ክፍል አንድ** ..... 4

በኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት አገልግሎት እና ለዜጎች የሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ..... 4

1.1 የኢትዮጵያ የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ዘርፍ የሚመራባቸው ህጎች ከዓለም አቀፍ ህጎች እና ድንጋጌዎች አኳያ ያላቸው አንድምታ ፣ ..... 5

1.2 ለዜጎች በቂ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች አለመሰጠታቸው ያስከተላቸው ዘርፈ ብዙ ችግሮች ፣ ..... 7

1.3 የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናው አስፈላጊነት ..... 9

**ክፍል ሁለት** ..... 13

የዜጎች መብት እና ግዴታዎች እና ስለ ዐረብ ሀገሮች መታወቅ ያለባቸው የጋራ ልምዶች እና ባህሎች ..... 14

2.1 በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት የተቀባይ ዐረብ ሀገሮች መገኛቸው እና አስፈላጊ መረጃዎች ..... 14

2.2 የዐረብ ሀገራት የጋራ የሆኑ ባህሎች እና ልማዶች ..... 16

2.3 ዜጎች ስለመብቶቻቸው እና ግዴታቸው ማወቅ ያለባቸው ጉዳዮች ..... 18

**ክፍል ሦስት** ..... 24

ወደ ዐረብ ሀገሮች ለሥራ ለሚሰማሩ ዜጎች የሚያስፈልጉ የዐረብኛ ቃላቶች እና የንግግር ሀረጎች ..... 24

3.1 መሰረታዊ የዐረብኛ ቋንቋ ቃላቶች ..... 25

3.2 ከዐረብኛ ንግግር የሚጠቀሙ ሀረጎች ..... 44

# መግቢያ

የኢትዮጵያ በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት አገናኝ ኤጀንሲዎች አሰሪ ፌዴሬሽን የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ዘርፍ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ይህን ሰነድ በማዘጋጀት በዐረብ ሀገራት በውጭ ሀገር የሥራ ሥምሪት አገናኝ ኤጀንሲዎች በኩል ለሚሄዱ የተለያዩ ዜጎች ስለ ሚሄዱባቸው የተለያዩ የመካከለኛው ምሥራቅ ዐረብ ሀገራት ስለ መግባቢያ ቋንቋቸው እና የተለያዩ ባህሎቻቸው እንዲሁም ከሥራቸው ጋር በተያያዘ ማወቅ ስለሚገባቸው ጉዳዮች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች እንዲሰጡ እና ዜጎች ወደ ዐረብ ሀገር ለሥራ ከመሰማራታቸው በፊት በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያግዛል፡፡ ይህ ሰነድ እ.ኤ.አ በ2021 (travel smart – work smart) በሚል ርዕስ በዓለም አቀፍ የሥራ ድርጅት ትብብር ከተዘጋጀው ሰነድ ለየት የሚልባቸው ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ከ ገፅ አንፃር ሰፊ ያልሆነ መሆኑ ፣ በእጅ ለመያዝ ቀላል እና አመቺ ከመሆኑም በተጨማሪ በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀ መሆኑ ዜጎች በቀላሉ አንብበው መረዳት ይችላሉ።
- ያካተታቸው ጭብጦች የተመጠኑ መሆናቸው እና ስለአብዛኞቹ በመካከለኛው ምሥራቅ ስለሚገኙ የዐረብ ሀገሮች በቂ ግንዛቤን ለመፍጠር እንዲቻል አስፈላጊ የሀገሮች መረጃ መካተታቸው።
- ዜጎች ወደ ዐረብ ሀገር ለሥራ ከመሰማራታቸው በፊት መሰረታዊ የዐረብኛ ቋንቋ ላይ ትኩረት በመስጠት አስፈላጊ ቃላቶችን እና ጠቃሚ የንግግር አገላለፆችን መያዙ።

ስለሆነም ይህ ሰነድ ወደ ዐረብ ሀገር የሚሄዱ ዜጎችን ለማብቃት እና ያለባቸውን የመረጃ ክፍተት ለመሙላት ስለሚያግዝ በኢትዮጵያ የሚገኙ በውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት የአገናኝ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ኤጀንሲዎች በእነሱ በኩል ዜጎች ወደ ውጭ ሀገር ከመላካቸው በፊት ይህን ሰነድ በመረዳት በቂ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ሰነድ በሦስት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን ክፍል አንድ ስለ ኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ዘርፍ እንዲሁም በውጭ ሀገር ሥራ ለሚሰማሩ ዜጎች በቂ ስልጠና ባለመሰጠቱ ዜጎች ላይ እየደረሱ ያሉ የመብት ጥሰቶች እና በኢትዮጵያ ዘርፉን አስመልክቶ ስለወጡ የተለያዩ አዋጆች ይዳስሳል ፤ ክፍል ሁለት

ደግሞ ስለዐረብ ሀገራት የጋራ ባህል እና ልምድ የኢትዮጵያ ዜጎች እንዲገነዘቡ በማድረግ መብት እና ግዴታዎቻቸውን ያስቀምጣል ፤ በክፍል ሦስት ደግሞ አስፈላጊ የሆኑ ከሥራቸው እና ከኑሯቸው ጋር የሚገናኙ የዐረብኛ ቋንቋ ቃላትን እና የመግባቢያ ሀረጎችን ይዳስሳል፡፡ ይህ ሰነድ በዋናነት ወደ ዐረብ ሀገራት በመሄድ ወደ ሥራ መሰማራት የሚፈልጉ ዜጎችን ለማብቃት በማሰብ በዘርፉ ሥልጠና ለመስጠት ፍቃድ የተሰጣቸው የማሰልጠኛ ተቋማት እና በአገናኝ ሥራ ላይ የተሰማሩ ኤጀንሲዎች ትኩረት ሰጥተው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን እንዲሰጡ ለማድረግ ነው፡፡

# የአሰልጣኞች ስልጠና መርሃ ግብር

| የሰነዱ ክፍሎች | ሰዓት | የሚፈጀው ጊዜ | ርዕሶች |
|---|---|---|---|
| ክፍል አንድ | 3:00 - 3:05 | 5 ደቂቃ | የሰነዱ ትውውቅ |
| | 3:05 - 3:30 | 25 ደቂቃ | የስደት የቃላት ፍቺዎች፣ የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት በኢትዮጵያ፣ እና ዓለም አቀፍ ህጎች እና ድንጋጌዎች |
| | 3:30 - 4:00 | 30 ደቂቃ | የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች በበቂ ሁኔታ ባለመስጠታቸው የተከሰቱ እና እየተከሰቱ ያሉ ችግሮች |
| | 4:00 - 4:30 | 30 ደቂቃ | ለዜጎች የሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች አስፈላጊነት |
| | 4:30 - 4:40 | 10 ደቂቃ | የቁርስ እረፍት |
| ክፍል ሁለት | 4:40 - 6:00 | 1 ሰዓት ከ20 ደቂቃ | የዜጎች መብት እና ግዴታዎች |
| | 6:00 - 6:30 | 30 ደቂቃ | የመካከለኛው ምሥራቅ ዐረብ ሀገራት የጋራ የሆኑ ልምዶች እና ባህሎች |
| | 6:30 - 8:00 | 1 ሰዓት ከ30 ደቂቃ | ምሳ ሰዓት |
| ክፍል ሦስት | 8:00 - 9:00 | 1 ሰዓት | ዜጎች ሊያቋቸው የሚገቡ መሰረታዊ የዐረብኛ ቃላቶች |
| | 9:00 - 9:10 | 10 ደቂቃ | የሻይ እረፍት |
| | 9:10 - 10:30 | 1 ሰዓት ከ20 ደቂቃ | ዜጎች ሊያቋቸው የሚገቡ የዐረብኛ ቋንቋ መሰረታዊ የንግግር ሀረጎች |
| | 10:30 - 10:45 | 15 ደቂቃ | ማጠቃለያ |

# ክፍል አንድ

## በኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት አገልግሎት እና ለዜጎች የሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች

### የሚከናወኑ ተግባራት

- *የሥልጠናውን ይዘት ማስተዋወቅ።*
- *ተሳታፊዎች በርዕሱ ዙሪያ ካላቸው ልምድ ተሞክሮዎችን እንዲያካፍሉ ማድረግ።*
- *አስፈላጊ የሆኑ በዘርፉ የምንጠቀምባቸውን ዋና ዋና ትርጓሜዎች ማብራራት።*

### ከስልጠናው በኋላ ተሳታፊዎች ፡

- *በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ዙሪያ መንግስት ያወጣቸውን የተለያዩ ህጎች እና አዋጆች የዜጎችን መብት እና ጥቅም በማስከበር በኩል የሚኖራቸውን ፍይዳ ያስረዳሉ፡፡*
- *የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ጋር በተያያዘ በውጭ ሀገር በሥራ ተሰማርተው የሚገኙ ዜጎች ላይ የሚከሰቱ የመብት ጥሰቶች ምክንያቶችን ይገልፃሉ፡፡*
- *በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ተሰማርተው ራሳቸውን፣ ቤተሰባቸው እና ሀገራቸውን መጥቀም ለሚፈልጉ ዜጎች መብታቸው እና ደህንነታቸው ተጠብቆ መሥራት እንዲችሉ የግንዛቤ መስጫ ስልጠናዎች ጥቅሞችን ይገልፃሉ፡፡*

## የቃላት ፍቺዎች

- **ስደት፡** *በዚህ ስልጠና ውስጥ ስደት ስንል ዓለም አቀፍ ስደትን ይመለከታል።*
- **ዓለም አቀፍ ስደት፡** *ምንም እንኳን የዓለም አቀፍ ስደት ትርጉም ጋር በተያያዘ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ሁሉም ሀገራት የተስማሙበት ትርጉም ባይቀመጥም ዓለም አቀፍ ስደት ስንል ሰዎች ከሀገራቸው ወጥተው ዓለም አቀፍ ድንበር ተሻግረው በሌሎች ሀገራት በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት የሚቆዩበትን ሁኔታ ነው፡፡*

- **የሥራ ስደት፡** የሥራ ስደት ስንል ሁለት አይነት ትርጉም የያዘ ሲሆን ሰፋ ያለው አረዳድ ማንኛውንም ሀገሩን ለቆ በውጭ ሀገራት በስደተኛ መጠለያ ያለ ወይም ደግሞ የሥራ ፈቃድ አግኝቶ እየሰራ ያለን አካል ያካትታል፡፡ ነገር ግን የተገደበ የሆነው አረዳድን ያየን እንደሆነ ለሥራ ብቻ መደበኛ በሆነም ሆነ መደበኛ ባልሆነ መንገድ ወደ ውጭ ሀገር የሚሰደዱ ዜጎችን ያካትታል፡፡
- ***ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር የሚሰማራ ሰራተኛ*** ፡ይህንን በተመለከተ የኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት አዋጅ 923/2016 አንቀፅ 1 ንዑስ አንቀፅ 4 ባስቀመጠው መሰረት በውጭ ሀገር ለሥራ የተሰማራ “ሰራተኛ” ማለት ህጋዊ በሆነ መነገድ ከሀገር ውስጥ ፈቃድ ያለው በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት አገናኝ ኤጀንሲ በኩል ወይም ደግሞ በውጭ ያለ ቀጣሪ ወኪል ጋር የሥራ ስምምነት ያለው ማለት ነው፡፡

## 1.1 የኢትዮጵያ የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ዘርፍ የሚመራባቸው ህጎች ከዓለም አቀፍ ህጎች እና ድንጋጌዎች አኳያ ያላቸው አንድምታ ፣

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት የመዘዋወር ነፃነት ከመሰረታዊ ዲሞክራሲያዊ መብቶች አንዱ መብት እንደሆነ በግልፅ አስቀምጧል፡፡ ዜጎች ይህንን በአንቀፅ (32) የተጠቀሰውን መብት በመጠቀም ብዙ ኢትዮጵያውያን ኑሯቸውን ለማቃናት እና ራሳቸውን ጠቅመው ቤተሰባቸውን ለመደገፍ በተለያዩ የዐረብ ሀገሮች በተለያየ የሥራ ዘርፍ ተሰማርተው ይገኛሉ፡፡ በቀድሞ አጠራር የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እ.ኤ.አ. በ 2008 እና በ 2014 መካከል በተለያዩ ገፊ እና ሳቢ ምክንያቶች በበርካታ ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በህገ ወጥ መንገድ እንደወጡ ይገልፃል። በተመሳሳይ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ 480,480 ኢትዮጵያውያን ብቻ በሕጋዊ መንገድ ወደ ዐረብ ሀገሮች ሄደዋል። ነገር ግን መንግስትም ሆነ በዘርፉ እየሰሩ የሚገኙ ተቋማት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ህጋዊ በሆነ መልኩ በውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት መሳተፍ ለሚፈልግ ሁሉ መንግስት በዘርፉ ያወጣቸውን ህጎችን በመከተል ዜጎች ከሀገር ወጥተው

በተለያየ የሥራ መስክ በመሰማራት ራሳቸውን ፣ ቤተሰባቸውን እና ሀገራቸውን እንዲጠቅሙ በማሰብ ብዙ ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛል፡፡

ዘርፉ እንደሀገር ከሚያስገኘው ገቢ አንፃር ልማትን የሚደግፍ በመሆኑ የተሻለ የሥራ ዕድል ወደሚገኝባቸው ሀገሮች ዜጎች ከሀገር ወጥተው በሚፈልጉት የሥራ ዘርፍ ተሰማርተው ራሳቸውን እና ቤተሰባቸውን ከመጥቀም ባለፈ ለሀገር የሚያስገቡት የውጭ ምንዛሬ ከፍተኛ ስለሆነ በብዙ የዓለም ሀገራት ተቀባይነት ያገኘም ጭምር ነው፡፡ በዚህ ዘርፍ ከሚታወቁት ዋና ተዋናዮቹ መካከል ቻይና ፣ ሜክሲኮ ፣ ህንድ እና ኢንዶኔዥያ ተጠቃሽ ናቸው።

የኢትዮጵያ መንግስትም ይህንን በመረዳት ሥራ አጥነትን ለመቀነስ እንዲሁም ህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከል በማሰብ ወደ ዐረብ ሀገሮች በቤት ሰራተኝነት እንዲሁም በሌሎች ሙያዎች ህጋዊ በሆነ መልኩ ወደ ሥራ መሰማራት እንዲችሉ እና መብታቸው እና ደህንነታቸው እንዲረጋገጥ የተለያዩ አዋጆችን አውጥቷል፡፡ እነዚህ አዋጆች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

| አዋጅ ቁጥር | ሥያሜ |
|---|---|
| 104/1998 | የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ አዋጅ |
| 632/2009 | የሥራ እና ሰራተኛ ማገናኘት አገልግሎት አዋጅ |
| 923/2016 | የኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት አዋጅ |
| 1246/2021 | የኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ማሻሻያ አዋጅ |
| 909/2015 | ህገወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በህገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ |
| 1178/2020 | በሰው የመነገድ እና ሰውን በሕገወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ |

ኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪትን በተመለከተ በሀገር ደረጃ ህጎችን ከማውጣት በተጨማሪ በዘርፉ የወጡ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ህጎች እና ድንጋጌዎችንም በመፈራረም

ለተግባራዊነቱ በትብብር እየሰራች ትገኛለች፡፡ ለምሳሌ ያክል እ.ኤ.አ. በ2018 የተፈረመውን የዓለም አቀፍ የፍልሰት ስምምነት (GCM) ተከትሎ፣ የኢትዮጵያ መንግስት የብሔራዊ የስደት ፖሊሲን አውጥቶ በዘርፉ መደበኛ የሰዎችን ስደት በመደገፍ እና የህገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመግታት ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት አገናኝ ኤጀንሲዎች አሰሪ ፌዴሬሽን የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ አጀንሲዎች የሚመሩበትን የስነ ምግባር ደንብ ከቀድሞ የሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከዓለም አቀፍ የሥራ ድርጅት ጋር በመተባበር ቀርፆ ሥራ ላይ እንዲውል አድርጓል፡፡

የተለያዩ ህጎችን ማፅደቅ እና ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር እንደ ሀገር በጋራ የመሥራቱ ሂደት እንዳለ ሆኖ ነገር ግን አሁንም ቢሆን የዜጎችን መብት፣ ጥቅም፣ ደህንነታቸውን እና ክብራቸውን በተጨባጭ ለማስጠበቅ በተለይም ወደ ዐረብ ሀገራት በቤት ሰራተኝነት የሚሰማሩ ዜጎች ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍና እንግልት ለማስቆም የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን አጠናክሮ መስጠት እንደሚገባ መረጃዎች ያመላክታሉ።

## 1.2 ከዜጎች በቂ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች አለመሰጠታቸው ያስከተላቸው ዘርፈ ብዙ ችግሮች ፣

ኢትዮጵያ ከሰሃራ በታች ከሚገኙ የአፍሪካ ሀገሮች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ዜጎችን በውጭ ሀገር ለሥራ በማሰማራት ትታወቃለች፡፡ ብዙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በየአመቱ ከተለያዩ ክልሎች በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በተለይ ደግሞ ሴቶች በባህረ ሰላጤው የዐረብ ሀገሮች በቤት ውስጥ ሥራ ለመሰማራት ወደ ውጭ ሀገር ይሰማራሉ፡፡ ይህ ወደ ውጭ ሀገር በሥራ ለመሰማራት የሚደረገው ጉዞ ህጋዊ በሆነ መልኩም ብቻ ሳይሆን ህገ ወጥ በሆነ መንገድም እንዲሁ በርካታ ዜጎች ከሀገር ይወጣሉ፡፡ አብዛኞቹ በዚህ መልኩ ከሀገር የሚወጡት ዜጎች በትምህርት ብዙም ያልገፉ፣ ለዘርፉ የሚያስፈልገውን መሰረታዊ የሙያ ክህሎት ለመቅሰም የሚቸገሩ ከመሆናቸውም በላይ ስለሚሄዱባቸው ሀገሮች የሥራ ሁኔታ፣ ስለመብታቸው እና ግዴታቸው፣ ስለጉዞው አጠቃላይ ሂደት፣ በውጭ ሀገሮች ሊያጋጥሟቸው

ስለሚችሉ ፈተናዎች ከዚህም ባለፈ ከሀገር ወጥተው ስለሚያሳኩት ዓላማ ግልፅ የሆነ ግንዛቤ የሌላቸው ናቸው፡፡

በዘርፉ የተሰማሩ እና ለዜጎች ስልጠና የመስጠት ኃላፍነት ያለባቸው የባለድርሻ አካላትም ወደ ውጭ ለሥራ ለሚሰማሩ ዜጎች በበቂ ሁኔታ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ባለመስጠታቸው በባህረ ሰላጤው ዐረብ ሀገራት በቤት ውስጥ ሥራ ላይ የተሰማሩ ኢትዮጵያውያን ዜጎች  በተለያዩ ደረጃዎች ሰብዐዊ መብታቸው ተጥሶ ለአካላዊ ጉዳት እና ስነልቦናዊ ችግሮች የሚጋለጡ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ኢትዮጵያውያን ዜጎች ላይ የሚደርሰው ዘርፈ ብዙ ግፍ እና ችግር ተባብሶ የቀጠለበት ሁኔታ ስለነበር መንግስት እ.ኤ.አ በ2013 ወደ ዐረብ ሀገሮች የሚደረገውን የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪትን በአዋጅ ማገዱ አይዘነጋም፡፡

ዜጎች ላይ ለሚደርሰው የመብት ጥሰት በዘርፉ በውጭ ሀገር በአገናኝ ሥራ ላይ የተሰማሩ ኤጀንሲዎችን እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሥራ ክፍሎች ጭምር የዜጎችን መብት፣ ጥቅም እና ደህንነት ከማስጠበቅ አኳያ ትኩረት ሰጥተው ባለመንቀሳቀሳቸው ዜጎች በተሰማሩበት ህጋዊ ሥራ ላይም ሆነው ለከፍተኛ ችግሮች እንዲጋለጡ አድርጓቸዋል፡፡ በተጨማሪም መንግስት ዘርፉን ለመምራት ያወጣቸው ፖሊሲዎችን እና ድንጋጌዎችን በአቅም ውስንነት ፣ አላስፈላጊ ህገወጥ አሰራሮች እና አሰልቺ የቢሮክራሲ ሂደቶች በመንሰራፋታቸው አፈፃፀማቸው ላይ የሚጠበቀውን ውጤት ማምጣት አልተቻለም፡፡ በዚህም ሳቢያ ዜጎች በቂ ግንዛቤ ሳይሰጣቸው ለሥራ ወደ ውጭ የሚሰማሩ በመሆናቸው ቀጥለው የተዘረዘሩት ዘርፈ ብዙ ችግሮች ይደርስባቸው እንደነበር ይታወቃል ፡፡

- በደላሎች በመታለል ወደ ውጭ ሀገር ለሥራ ለመሰማራት ህጋዊ ያልሆነ ክፍያ እንዲፈጽሙ መገደድ፣
- ደመወዛቸውን  በወቅቱ ያለማግኘት እና አንዳንዴም ደመወዝ የመቀነስ ሁኔታዎች መፈጠር፣
- ከሥራ ውሉ ስምምነት ውጭ ረዥም ሰዓታትን በሥራ እንዲያሳልፉ መገደድ፣

- እረፍት እና ፍቃድ ያለማግኘት፣
- በሥራ ላይ ስድብ፣ ጥላቻ፣ አካላዊ ቅጣት እንዲሁም አልፎ አልፎ ፆታዊ ጥቃት መድረስ፣
- የጤና ዋስትና ያለማግኘት፣
- ለሰው ልጅ መሰረታዊ የሆኑ ፍላጎቶችን በበቂ ሁኔታ ያለማሟላት፣

## 1.3 የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናው አስፈላጊነት

በዘርፉ በአገናኝ ሥራ ላይ የተሰማሩ ኤጀንሲዎች እና በማሰልጠኛ ተቋማቶች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ዜጎች በውጭ ሀገር ለሥራ ከመሰማራታቸው በፊት የቅድመ ጉዞ ስልጠናዎችን እንዲሰጡ መንግስት አቅጣጫ ቢያስቀምጥም የሚሰጡት ስልጠናዎች የይስሙላ እና ዜጎች ላይ በቂ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ባለመሆናቸው አሁንም ድረስ ዜጎች ላይ የሚደርሰው የሰብዐዊ መብት ጥሰቶች አልቆሙም፡፡ ስለሆነም ልክ እንደ ፊሊፒኖች፣ ኢንዶኔዥያ እና ሌሎች የኢስያ ሀገር ተወላጆች ኢትዮጵያውያን ዜጎች በሚሰማሩበት ሙያ በቂ እውቀት ኑሯቸው የሚሰማሩባቸው የዐረብ ሀገራት ህጎችን፣ ደንቦችን፣ ባህሎችን፣ ልማዶችን እንዲሁም መብት እና ግዴታቸውን አውቀው ተከብረው እና መብትና ጥቅማቸው ተረጋግጦ እንዲሰሩ ለማድረግ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ተጠናክረው መሰጠት መቻላቸው ዜጎች ላይ የሚደርሱ ዘርፈ ብዙ የሰብዐዊ መብት ጥሰቶችን መከላከል ይቻላል፡፡

### 1ኛ) ዜጎች ስለ ህጋዊ የሥራ ስምሪት በጎ አመለካከት እንዲኖራቸው ማድረግ ፣

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ዜጎች ህጋዊ በሆነ መንገድ በውጭ ሀገር ለሥራ ቢሰማሩም የሰብዐዊ መብት ጥሰቶች እየተፈፀሙባቸው ይገኛል፡፡ በእዚህም ሳብያ ዜጎች ስለ ህጋዊ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ያላቸው በጎ አመለካከት እየቀነሰ ስለሄደ ዜጎች ወደሀገራቸው ተመልሰው ዳግምኛ ወደ ውጭ ሀገር ለመውጣት የህገወጥን መንገድ እንዳማራጭ ሲጠቀሙ ይታያሉ፡፡ ከዚህም ባለፈ አንዳንድ ለውጭ ሀገር ሥራ በአገናኝ ሥራ ላይ የተሰማሩ ኤጀንሲዎች ህጋዊ

የሙያ ፈቃዳቸውን ሺፋን በማድረግ ህገወጥ በሆነ መልኩ ዜጎችን ለማሰማራት የሚንቀሳቀሱም አሉ፡፡ ስለሆነም ዜጎች ህጋዊ በሆነ መልኩ ወደ ውጭ ሀገር ሲሰማሩ ስለ ውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት በቂ መረጃ በመስጠት እና እንዳይጭበረበሩ ለማድረግ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን በመስጠት ዜጎች ስለህጋዊ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ጥሩ አመለካከት እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 2፣) መብት እና ግዴታዎችን ጠንቅቀው እንዲያውቁ ማድረግ ፣

ዜጎች ከሀገር ከመውጣታቸው በፊት ስለ መብታቸው እና ግዴታቸው ጠንቅቀው ማወቃቸው ኃላፊነታቸውን በሚገባ ለመወጣት እና መብታቸውን ለማስከበር ይረዳቸዋል፡፡ዜጎች መብታቸውን እና ግዴታቸውን አውቀው ከወጡ ሊደርስባቸው ከሚችሉ የሰብዐዊ መብት ጥሰቶችን፣ ፆታዊ ጥቃትን፣ እና ሌሎች ከባድ እና አስከፊ ችግሮችን መከላከል ይችላሉ፡፡ መብታቸውን እና ግዴታቸውን ጠንቅቀው እንዲያውቁ ማድረግ ስንል ሁሉንም የጉዞ ሂደቶች ያካተተ ሲሆን ከነዚህም መካከል፤

- በውጭ ሀገር ሥራ ከሚያሰማራቸው ኤጀንሲ ጋር በተያያዘ በውጭ ሀገር ሥራ ለመሰማራት ዜጎች የሚከፍሉት ክፍያ እንደሌለ፤ ስለሚሰማሩበት ሥራ በቂ የሆነ መረጃ የመስጠት ግዴታችውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡ ለሥራው በሚሰማሩ ዜጎች በኩል ደግሞ በውጭ ሀገር ለሥራ መሰማራት ሲፈልጉ ማንነታቸውን የሚገልፅ ትክክለኛ መረጃዎችን የመስጠት ኃላፊነት እንዳለባቸው ማስገንዘብ፡፡
- ዜጎች ስለሚፈርሙት የሥራ ውል በሚገባቸው ቋንቋ የመረዳት እና ውስጡ ስላሉ የተለያዩ መብቶች እና ግዴታዎች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማስቻል፡፡
- ዜጎች በሥራ ከተሰማሩም በኋላ ስለተሰማሩባቸው ሀገሮች ህጎች የመረዳት፣ ሥራን በአግባቡ የመሥራት እና ከተሰማሩበት ቦታ ወደ ሌሎች ቦታዎች ያለመሰወር ግዴታዎች እንዳሉባቸው ማስገንዘብ፡፡

- ዜጎች ላይ የተለያዩ ችግሮች ቢደርስባቸው ህግን ተከትለው በምን አይነት መልኩ ሪፖርት ማድረግ እንደሚችሉ እና መውሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች ቅድመ ግንዛቤ መፍጠር፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ዜጎች በቂ ግንዛቤ ኑሯቸው ከሀገር ወጥተው እንዲሰማሩ መደረጋቸው ዜጎች ያለምንም ችግር ዓላማቸውን አሳክተው ከራሳቸው አልፈው ቤተሰባቸውን እና ሀገራቸውን መጥቀም ይችላሉ፡፡ ወደ ሀገራቸውም ሲመለሱ በቀላሉ ከማህበረሰቡ ጋር መዋሀድ እና የራሳቸውን ኑሮ ለመምራት የሚያስችል ስነልቦና ኑሯቸው ህይወታቸውን መምራት ይችላሉ፡፡

## 3.5) በቋንቋ እና በባህል ልዩነቶች ምክንያት የሚከሰቱ ችግሮችን መቅረፍ ፣

በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ወደ ሥራ የሚሰማሩ ዜጎች በትምህርት ደረጃቸው በአብዛኛው በትምህርት ያልገፉ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በሥራ ስለሚሰማሩባቸው የዐረብ ሀገሮች ቋንቋ ምንም አይነት ግንዛቤ ሳይኖራቸው ከሀገር ስለሚወጡ በተለያዩ አጋጣሚዎች በሚፈጠሩ አለመግባባቶች እና ግጭቶች ምክንያት በአሰሪዎቻቸው ከስድብ አልፎ እስከ አካላዊ ቅጣቶች የደረሰ እርምጃዎች ይወሰድባቸዋል፡፡ ዜጎች በመጀመሪያ ደረጃ የሚሄዱባቸውን ሀገራት በትክክል ከማወቅ ጀምሮ የሚሄዱባቸውን ሀገሮች ቋንቋ፣ ባህል እና ልማዳቸውን ማወቅ ሥራቸውን በትክክል መሥራት እንዲችሉ እና ላላስፈላጊ ስድብ፣ ጥላቻ እንዲሁም አካላዊ ቅጣት አይዳረጉም፡፡

### የመረጃ ምንጮች ፡

*Assessment of Awareness Raising Interventions to Prevent Irregular Migration, MoLSA and ILO Country Office Report, 2018.*

*Emebet Kebede, Ethiopia: An assessment of the International Labour Migration Situation, the case of female labour migrants, GENPROM Working Paper, No.3*

*Shattered Dreams and Return of Vulnerability: Challenges of Ethiopian Female Migration to the Middle East, IS Academy Policy Brief No. 18,*

*Towards safer recruitment of Ethiopian women into domestic work abroad, early findings from the Meneshachin 'Our Departure' qualitative study, May 2022.*

# የቅድመ ጉዞ ስንቅ በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ለመሰማራት ፍላጎት ላላቸው ዜጎች

## ☞የዐረብ ሀገሮች የጋራ ልማዶች እና ባህሎች

## ☞የዜጎች መብት እና ግዴታዎች (ከሀገር መውጣት ጀምሮ እስከ መመለስ)

## ☞ወደ ዐረብ ሀገር ለሥራ ለሚሰማሩ ዜጎች የሚያስፈልጉ የዐረብኛ ቃላቶች እና አገላለፆች



የኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት አገናኝ ኤጄንሲዎች ፌዴሬሽን
2015

# ክፍል ሁለት

## የዜጎች መብት እና ግዴታዎች እና ስለ ዐረብ ሀገሮች መታወቅ ያለባቸው የጋራ ልምዶች እና ባህሎች

**የሚከናወኑ ተግባራት**

- የሥልጠናውን ይዘት ማስተዋወቅ
- ተሳታፊዎች በርዕሱ ዙሪያ ካላቸው ልምድ ተሞክሮዎችን እንዲያካፍሉ ማድረግ
- ስለዜጎች መብትና ግዴታዎች እንዲሁም የዐረቦች የጋራ ባህሎች ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያካፍሉ ማድረግ

**ከስልጠናው በኋላ ተሳታፊዎች ፡**

- ዜጎች ስለ ገልፍ ሀገሮች የጋራ የሆኑ ልምዶችን እና ባህሎች ማወቅ ያለባቸውን ጉዳዮች ይገልፃሉ፡፡
- በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት የሚሰማሩ ዜጎች ከሀገራቸው ከመውጣታቸው በፊት እና በኋላ ማወቅ የሚጠበቅባቸውን ጉዳዮች ያስረዳሉ፡፡
- ዜጎች በውጭ ሀገር ሲሰማሩ ያላቸው መብቶች እና ግዴታዎችን እንዲሁም ከሥራ ውሉ ጋር በተያያዘ ሊያውቁ የሚገባቸውን ጉዳዮች ያብራራሉ፡፡

## 2.1 በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት የተቀባይ ዐረብ ሀገሮች መገኛቸው እና አስፈላጊ መረጃዎች

በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ዜጎች በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት የሚሰማሩባቸው ሀገሮች መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ የሚገኙ ሀገሮች ሲሆኑ ዐረብኛ ቋንቋ ብሔራዊ ቋንቋቸው ሲሆን በእምነት በኩል በአብዛኛው የእስልምና እምነት ተከታዮች ናቸው። ኢትዮጵያውያን ዜጎች በውጭ ሀገር ሥራ የሚሰማሩባቸው የባህረ ሰላጤው ሀገሮች ከኢትዮጵያ ጋር የሁለትዮሽ ስምምነት በማድረግ እስከ አሁን የኢትዮጵያ ዜጎችን ሲቀበሉ የነበሩ ሀገሮችን እና እንዲሁም ለመቀበል ፍላጎቱ ያላቸውን ሀገሮች ዝርዝር መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## የባህረ ሰላጤው የዐረብ ሀገራት መገኛ እና ሌሎች መረጃዎች

| ተ.ቁ | የሀገራቱ ስያሜ | በዐረብኛ | የህዝብ ቁጥር፣ ሀይማኖት፣ ቋንቋ፣ መገበያያ ብር፣ የስልክ ቁጥር ኮድ | ዋና ከተማ | የአየር ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሳዑዲ | ሳዑዲ ዐራቢያ | 35.34 ሚሊየን ፣ እስልምና ፣ ዐረብኛ፣ ሳውዲ ሪያል፣ +966 | ሪያድ | ሞቃታማ ታህሳስ፣ ጥር እና የካቲት ቀዝቃዛ የአየር ንብረት |
| 2 | የተባበሩት ዐረብ ኤምሬት | አል ኢማራት | 9 272 000 ሚሊዮን ፣ እስልምና፣ ዐረብኛ፣ ኢማራት ዲርሀም ፣ +971 | አቡ ዳቢ | ታህሳስ፣ ጥር፣ የካቲት እና መጋቢት ቀዝቃዛ አየር ንብረት |
| 3 | ኳታር | ቀጠር | 3 059 000 ሚሊየን ፣ እስልምና፣ ዐረብኛ፣ ካታሪ ሪያል፣ +974 | አደውሐ | ሚያዝያ፣ ግንቦት፣ ጥቅምት እና ህዳር ቀዝቃዛ አየር ንብረት |
| 4 | ባህሬን | በህሬይን | 1 442 000 ሚሊየን ፣ እስልምና፣ ዐረብኛ፣ ባህሬን ዲናር፣ +973 | ማናማ | ታህሳስ፣ ጥር፣ የካቲት፣ መጋቢት ቀዝቀዝ ያለ አየር ንብረት |
| 5 | ኩዌት | ኩዌት | 4 467 000 ሚሊየን፣ እስልምና፣ ዐረብኛ፣ የኩዌት ዲናር፣ +965 | ኩዌት ከተማ | መጋቢት እና ሚያዝያ ቀዝቀዝ ያለ የአየር ንብረት |
| 6 | ኦማን | ኡማን | 4 674 000 ሚሊየን፣ እስልምና፣ ዐረብኛ፣ የኦማን ሪያል፣ +968 | መስቀጥ | ታህሳስ፣ ጥር እና የካቲት ቀዝቀዝ ያለ የአየር ንብረት |
| 7 | ጆርዳን | ጆርዳን | 11 192 000 ሚሊየን፣ እስልምና፣ ዐረብኛ፣ የጆርዳን ዲናር፣ +962 | አማን | ታህሳስ እና ጥር ቀዝቃዛ ወራት |
| 8 | ሌባኖስ | ሉብናን | 6 685 000 ሚሊየን፣ እስልምና፣ ዐረብኛ፣ የሌባኖስ ፓውንድ፣ +961 | ቤሩት | ጥር የካቲት እና መጋቢት አጋማሽ ቀዝቃዛ የአየር ንብረት |
| የህዝብ ቁጥር እና ሌሎች መረጃዎች ምንጭ ፡ www.britannica.com እና www.google.com | | | | | |

## 2.2 የዐረብ ሀገራት የጋራ የሆኑ ባህሎች እና ልማዶች

ዜጎች በውጭ በተለያዩ የዐረብ ሀገራት ለሥራ ከመሰማራታቸው በፊት ስለሚሄዱባቸው ሀገራት ባህላዊ ገፅታዎችን፣ ልማዶችን እና የእምነታቸው መገለጫዎችን ጠንቅቀው እንዲረዱ ማድረግ ራሳቸውን ከተለያዩ ሁነቶች ጋር አጣጥመው ለመኖር እና መልካም የሥራ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል፡፡ ስለሆነም ቀጥለው የተዘረዘሩ ዋና ዋና የዐረብ ሀገራት የጋራ የሆኑ ባህሎች፣ ልማዶችን እና የእመነት መገለጫዎቻቸውን ማሳወቅ ተገቢ ይሆናል፡፡

- በዐረቦች የእስልምና ሀይማኖት እና የሰዎች የአኗኗር ዘይቤ ትልቅ ቁርኝት አላቸው።
- የእስልምና ተከታዮች በቀን አምስት ጊዜ የፀሎት ወቅት አላቸው፡፡ ወንዶች የቤተሰቡ አካላት ወደ መስጊድ በመሄድ እምነታቸውን ሲያከናውኑ ሴቶች ደግሞ ባብዛኛው በቤታቸው ይሰግዳሉ፡፡በቤታቸው በሚሰግዱበት ወቅት ከፊት ለፊት መቆም፣ ማቋረጥ እና አፍጥጦ ማየት የተከለከለ ነው፡፡
- የዐርብ ቀን ፀሎት ወይም ስግደት ግን እንደ በዓል ስለሚቆጠር ሁሉም የቤተሰቡ አካል ሴቶችንም ጨምሮ የሚያግዳቸው (የወር አበባ ላይ መሆን ወይም ህመም) እስካላጋጠማቸው ወደ መስጊድ በመሄድ ይሰግዳሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ያለአሰሪዎች ፈቃድ የእምነት መገለጫቸውን እንደ ቁዱስ ቁርአን ወይም መስገጃዎች መንካት የተከለከለ ነው፡፡
- የረመዳን ፆም ሌላው ዋናው የእመነታቸው መሰረታዊ ተግባር ሲሆን ሌሊት ከሱብሂ ሰላት ወቅት በፊት ምግብ (ሱሑር) ምግብ ከበሉ በኋላ ቀኑን ሙሉ የመግሪብ ወቅት ሰላት እስከሚደርስበት ጊዜ ምግብም ሆነ መጠጥ ስለማይወስዱ ፊትለፊታቸው ሆኖ ምግብ መብላት የተከለከለ ነው፡፡
- ለአቅመ አዳም የደረሱ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ከቤተሰቡ አባላት ውጭ ካሉ ተቃራኒ ፆታዎች ጋር ብቻቸውን እንዲሆኑ አይፈቀድላቸውም።

- ሰላምታ ብዙ ጊዜ የሚገልፁት እርስ በእርስ በመጨባበጥ ሲሆን የሚተቃቀፉት ደግሞ ቅርብ የሚሉትን አካላት ነው።
- ዐረቦች በሀይማኖታቸው የማይፈቀዱ ምግቦችን አይመገቡም።
- ምግብ የሚበላው በቀኝ እጅ ሲሆን ስጦታም ሲሰጡ በቀኝ እጃቻቸው ይሰጣሉ።
- ምግብ እየተበላ ወሬ ማውራት የተለመደ አይደለም።
- የአልኮል መጠጦችም ክልክል ናቸው።
- ቤቶች ውስጥ ሲገቡ ጫማ ውጭ ላይ አስቀምጠው የመግባት ልምድ አላቸው።
- ብዙ ግዜ በቤተሰብ መካከል የሚኖሩ ጫወታዎች እና ትውውቆች ከ እራት በፊት ያደርጋሉ።
- ከአለባበስ ጋር በተያያዘ ወንዶች አጭር ሱሪ ፤ ሴቶች ደግሞ እግር እና እጆቻቸውን የሚያሳዩ ልብሶችን አይለብሱም። የተለመደው አለባበስ ሴቶች ሙሉ ሰውነታቸውን አባያ በተባለ ልብስ የሚሸፍኑ ሲሆን፤ ፀጉራቸውን ደግሞ በሂጃብ ይሸፍናሉ፡፡ ስለሆነም ለሥራ ወደ ዐረብ ሀገር የምትሰማራ ሴት አለባበስ ልምዳቸውን አውቃ ተግብራ መሄድ ይኖርባታል፡፡
- በአቀማመጥ ዙሪያ ከሌሎች ሰዎች ከፍ ብሎ መቀመጥን እንዲሁም ወይም እግር ዘርግቶ መቀመጥ የተወደደ አይደለም። ከዚህም በተጨማሪ የታችኛውን የግር ክፍልም ማሳየት የተከለከለ ነው፡፡
- በንግግር ሰዓት በጣም ከፍተኛ ድምፅ ማውጣት ወይም መጮህ ለሴቶች የተወደደ አይደለም። ነገር ግን እንደ ዐረቦች ባህል ወንዶች ከፍ ባለ ድምፅ መናገራቸው የማንነታቸውን ክብር ማሳያ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡
- ከቤተሰብ ወይም ዝምድና ካላቸው ሰዎች ውጭ ሰላምታ ማቅረብ፣ በእጅ መጨበጥ ወይም ከሥራ ውጭ አንድ ላይ ማውራት የተፈቀደ አይደለም።
- ተቃራኒ ፃታ ጋር አላስፈላጊ እይታ ወይ እንቅስቃሴዎችን ማሳየት የተከለከለ ነው።

- የጋብቻ ምሥክር ወረቀት ካላቸው ባለ ትዳሮች በስተቀር በዐረብ ሀግራት ወንድ እና ሴት ጥንድ ሆኖ መሄድ የተከለከለ ነው፡፡
- ስለቤተሰብ ሁኔታ ወይም ስለሚስት ጥያቄዎችን ማንሳት የተከለከለ ነው።
- ወደ ሥራ እየተቻኮለ ያለውን ሰው አቁሞ ለማናገር መሞከር ክብር አለመስጠት ነው።
- ወደ ሰዎች ጣትን መቀሰር የተከለከለ ነው።
- ዐረቦች በአብዛኛው የሚመገቡት የምግብ አይነቶች ውስጥ እንደዳቦ (ኹብዝ)፣ ሩዝ በሥጋ የዘወትር ምግቦቻቸው ናቸው፡፡ ማዕድ ላይ ያለውን የሌለውን አግበስብሶ መብላት ደግሞ የተለመደ አይደለም።
- ከእውነት በማይተናነስ መልኩ ለክብር ትልቅ ግምት ይሰጣሉ። ስለሆነም ከወንድ አሰሪ ጋር በሚወራበት በመተናነስ ፊት ፊቱን አለማየት እና አለባበስ ላይ ባህሎን የጠበቀ መሆን ይሆንበታል፡፡ ለሴት አሰሪም እንዲሁ ተገቢውን ክብር መስጠት እና እየቀደሙ አለማውራት፡፡

## 2.3 ዜጎች ስለመብቶቻቸው እና ግዴታቸው ማወቅ ያለባቸው ጉዳዮች

### ዜጎች ከሀገር ከመውጣታቸው በፊት የሚከተሉትን ጉዳዮች ጠንቅቀው ማወቅ አለባቸው

- ከሀገር የሚወጡበትን ዓላማ ጠንቅቀው ማወቅ፡ እንደሚታወቀው ዜጎች ከሀገራቸው ወጥተው በውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ለመሰማራት የሚወስኑት በብዙ ሳቢ እና ገፊ ምክንያቶች ነው፡፡ ነገር ግን ምክንያቶቹ እንዳሉ ሆኖ ውሳኔ ላይ የደረሱበትን አካሄድ በማጤን በመገምገም ማንም ጫና ሳይደርግባቸው ከራሳቸው በመነጨ ሰርቶ የመለወጥ እና ወገናቸውን የመጥቀም ፍላጎታቸው ከሆነ ህጋዊ በሆነ መንገድ የጉዞ ሂደቱን መጀመር ይችላሉ፡፡

- ለጉዟቸው እንዲሁም በሥራ ለመሰማራት የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ሰነዶችን ምንነት መገንዘብ እና ማወቅ፤
- ህጋዊ ፈቃድ ካለው በውጭ ሀገር የሥራ ሥምሪት በአገናኝነት ከተሰማራ ኤጀንሲ በኩል ለሥራ መሰማራት፤
- በውጭ ሀገር ሥራ ለመሰማራት ለኤጀንሲው የሚከፈል ምንም አይነት ክፍያ እንዴሌለ ማወቅ፤
- ቀኑ ያላለፈበት ወይም የታደሰ ፓስፖርት መያዝ፣ የመጣላቸው ቪዛ የሥራ ቪዛ መሆኑን ማረጋገጥ እንዲሁም የጤና ምርመራ ውጤት መያዝ፤
- የሥራ ውሉ ላይ የሚከፈላቸውን የደሞዝ መጠን እንዲሁም አጠቃላይ ስለሥራው ሁኔታዎች የተገለፁ ጉዳዮችን አይቶ መፈረም፤
- በሥራ የሚያሰማራቸውን የኤጀንሲ ሥም እና አድራሻ እራሳችውም ሆነ ቤተሰባቸው መዝግበው እንዲይዙት ማድረግ፤
- አስፈላጊ የጉዞ ሰነዶችን እንደፓስፓርት፣ የሥራ ውል እና ሌሎች መረጃዎችን ፎቶ ኮፒ አድርጎ መያዝ እና ለአደጋ ተጠሪ መስጠት፤
- የበረራ ቲኬታቸው ላይ ያሉ ማናቸውን ጠቃሚ መረጃዎችን በደንብ ማወቅ፤
- ስለበርራ እና ከአየርመንገዱ ጋር ተያይዞ ማወቅ ስላለባቸው
- ከሥራቸው ጋር የሚገናኙ መሰረታዊ የዐረብኛ ቋንቋ ቃላቶችን እና የንግግር ሀረጎችን መለማመድ፤
- የሙያ ስልጠናዎችን በመውሰድ በሚሰማሩበት የሙያ ዘርፍ የሙያ ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት (CoC) መያዝ፤
- ዜጎች ወደ ሥራ ስለሚሰማሩባቸው ሀገሮች ከሚልካቸው ኤጀንሲ ጋር ስለአሰሪው ሙሉ መረጃዎችን የማግኘት፤

- *ወደ ሥራ ከመሰማራታቸው በፊት ስለ ሥራው አይነት፤ ስለ ኑሮው ሁኔታዎች እና ስለ ሚሄዱበት ሀገር ልማዶች እና ወጎች በውጭ ሀገር ያሉ ሰዎችን መጠየቅ፤*

**ዜጎች ከሀገር ከወጡ በኋላ የሚከተሉትን ጉዳዮች ጠንቅቀው መገንዘብ ይኖርባቸዋል ፤**

- *በውጭ ሀገር ለሥራ ሲሰማሩ ቢያንስ በ 3 ወራት ውስጥ የመኖሪያ (ኢቃማ) እና የስራ ፈቃድ ከአሰሪው ጋር በመነጋገር ማውጣት፤*
- *የተገኘውን የመኖሪያ እና የሥራ ፈቃድ ጊዜው ከማለፉ በፊት ማሳደስ፤*
- *በውጭ ሀገር ያለን የኢትዮጵያን ቆንፅላ አድራሻ እና ስልክ መዝግቦ መያዝ፤*
- *የፓስፖርት፣ ስልክ፣ የሥራ ውል እንዲሁም ሌሎች ማስረጃቸውን ቅጅዎች መያዝ ፤*
- *መብት እና ግዴታን ጠንቅቆ ማወቅ፤*
- *ፓስፖርት ወይም ሌሎች መረጃዎች ጊዜ እንዳያልፍባቸው ተከታትሎ ማየት፤*
- *በመዳረሻ ላለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ አድራሻን በመንገር መመዝገብ፤*
- *በሥራ ቦታ የተለየ ችግር ሲያጋጥም እና ችግሮች የማይፈቱ ሲሆን በተቀባይ ሀገር ላለው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ማሳወቅ፤*

**ዜጎች በውጭ ሀገር ለሥራ ከተሰማሩ በኋላ በሚሰሩባቸው ሀገሮች መብቶች እና ግዴታዎች ስላላቸው ጠንቅቀው ሊያውቋቸው ይገባል ፤**

## በውጭ ሀገር የተሰማሩ ዜጎች መብቶች....

- *በሥራ ቅጥር ዉሉ መሰረት ስለሚሰሩት የሥራ አይነት፣ የሚሰሩበትን ቤተሰብ እና ሌሎች መረጃዎች የማወቅ፤*
- *ከሥራ ኮንትራት ውሉ ውጭ በሌላ ግለሰብ ቤት ያለመስራት፤ በንግግር ከሥራ ሰአት ውጭ ተስማምተው ከሰሩ ደግሞ ለተጨማሪው ሰአት ክፍያ መጠየቅ፤*

- የሰራተኞች ደሞዝ መታሰብ የሚጀምረው በውጭ ሀገር እግራቸው ካረፈበት ጀምሮ መሆኑን ማወቅ፤
- የሰሩበትን ደመወዝ በወቅቱ የመቀበል፣
- ተመጣጣኝ ምግብ፣ ምቹ መኖርያ እና ለስራው አስፈላጊ የሆኑ አልባሳትን የማኘት፤
- የአካላዊ ጉዳቶችም ሆነ ሌላ አደጋ ሲደርስ የጤና ዋስትና የማግኘት፣
- ከቤተሰቦቻቸው ጋር በስልክ ወይም በማህበራዊ ሚድያ የመገናኘት፣
- የሙብት ጥሰቶች ሲኖሩ ቅሬታ የማቅረብ፣
- የመኖሪያ እና የሥራ ፈቃድ በአሰሪው በኩል የማግኘት፣
- ፓስፖርት፣ የሥራ እና የመኖሪያ ፈቃድን እራስዎ ጋር የመያዝ ውይም ኮፒ አድርጎ መያዝ፣
- ሥራ ውሉ ላይ የተጠቀሰውን የሥራ አይነት ብቻ የመሥራት፣
- ሰብዓዊ ክብር የማግኘት፣
- የሥራ ውል ሲጠናቀቅ የወር ደሞዝን
- የሥራ ኮንትርራት ውሉ ሲያበቃ የመመለሻ የአውሮፕላን ቲኬት በአሰሪው እንደሚሸፈን ማወቅ፤

## በውጭ ሀገር የተሰማሩ ዜጎች ግዴታዎች …

- የምትሄዱበት ሀገራት ምነትን የሚፃረሩ ወይም ደግሞ ህጋዊ ያልሆኑ ድርጊቶች ላይ አለመሳተፍ፤
- ጥንቃቄ ለሚያስፈልጋቸው እና ውድ ለሆኑ እቃዎች እና ንብረቶች ልዩ ትኩረት መስጠት፤
- ወደ ሥራ የሚሰማሩበትን ሀገር ህግ፣ ባህል እና ልምድ ማክበር፣
- ሥራን አውቆ በአግባቡ መሥራት፣
- ሀቀኛ መሆን፣
- በአሰሪዎቻቸውም ላይ ሆነ ቤተሰቦቻቸው ላይ ተገቢ ያልሆኑ ነገሮችን ያለመፈፀም፤

- ከተቀጠሩበት አሰሪ ውጪ ለሌላ አካል ያለመስራት፣
- ከአሰሪው እና ቤተሰቦቹ ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር፣
- የሥራ ውሉን የጣሰ እስካልሆነ ድረስ በአሰሪው የሚሰጡ ትዕዛዞችን የማክበር፣
- የአሰሪውንም ሆነ አብረው የሚኖሩ የቤተሰብ አካላትን ሚስጥር መጠበቅ፣
- የአሰሪውን ንብረቶች ደህንነታቸውን መጠበቅ እንዲሁም ሳያስፈቅዱ አለመጠቀም፣
- ለሚዘጋጁ ምግቦች እንዲሁም የልጆች አያያዝ ላይ ተገቢውን ንፅህና መጠበቅ፤
- በግል ንፅህና በኩል ከምንገዜውም በላይ ትኩረት መስጠት፤
- የከፍላቸውንም ሆነ የአካባቢያቸውን ንፅህና መጠበቅ፤
- ሁልግዜ ተገቢ የሆነ የሰውነት ቅርፅን የማያሳይ አለባበስ መልበስ፤
- ገንዘብ ወደ ሀገር ቤት መላክ ሲፈለግ ህጋዊ በሆነ መልኩ መላክ ወይም ደግሞ በኢትዮጵያ ወደከፈቱት የባንክ ሂሳብ ገቢ ማድረግ፤

## ዜጎች በሥራ በተሰማሩባቸው ሀገሮች ውስጥ ከባድ የሆነ ነገር ከገጠማቸው ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች በማጤን መተግበር ይገባቸዋል ፤

- የሥራ ጫና ካለባቸው ከአሰሪዎቻቸው ጋር በውይይት መፍታት፤
- ሊያረጋጉ የሚችሉ የመዝናኛ ፕሮግራሞችን በረፍት ሰአታቸው ማየት፤
- ዝምተኛ እና አይናፋር ያለመሆን እና ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት ቅርብ ሰዎችን ማማከር፤
- ተስፋ አለመቁረጥ፣ መረጋጋት እና አለመበሳጨት
- ከችግሩ እንዴት መውጣት እንደሚችሉ ብቻ ማሰብ፣
- የአደጋ ጊዜ የስልክ ጥሪዎችን መጠቀም፤
- ለኤንባሲ፣ ለላኪ ኤጀንሲ ወይም ለዘመድ ስልክ መደወል፣
- ስልክ ማግኘት ካልተቻለ ከጎረቤት እርዳታ መጠየቅ፣

## የሥራ ውል ስምምነትን በተመለከተ ዜጎች በውጭ ሀገር ሥራ ከመሰማራታቸው በፊት ስለሚፈራረሙት የሥራ ውል በቂ ግንዛቤ ኑሯቸው እንዲፈርሙ የሚከተሉትን ነጥቦች በደንብ ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል ፣

- የሥራ ውሉ ላይ ያሉትን ነጥቦች በሙሉ በሚገባቸው ቋንቋ እንዲያነቡ ወይም እንዲነበብላቸው ማድረግ እና መፈረም፤
- የሥራ ውሉ ስለ ሚሰራው ሥራ፣ የሥራ አይነት፣ የደሞዝ መጠን፣ የሥራ ውሉ ስለሚቆይበት እና ስለሚያበቃበት ጊዜ፣ ስለ እረፍት ቀናት፣ ስለ ጉዞ ወጭዎች፣ ስለ ጤና ዋስትና እና ውሉ ሲያልቅ ስለመመለስ በደንብ መገንዘብ፤
- የሥራ ዉሉ ከተፈረመ በኋላ ስለሚፀናበት ጊዜ ማወቅ፤
- በአሰሪው ምክንያት ውሉ የሚቋረጥ ከሆነ ለመመለስ የሰራተኛው የጉዞ ወጭ የሚሸፈነው በአሰሪው እንደሆነ ማወቅ፤
- ውሉ በአሰሪና በሰራተኛው ሥምምነት ሊቋረጥ እንደሚችል መገንዘብ፤
- በራስ ፈቃድ ከሚሰሩበት ሀገር ለመመለስ የፈለገ ወጭውን ሰራተኛው እንደሚሸፍን ማወቅ፤
- ከሁለት አመት የኮንትራት ውል በኋላ ውሉ ከተራዘመ ሰራተኛው በሥራው መቆየት እንደሚችል ማወቅ፤

## የመረጃ ምንጮች


- የኢትዮጵያ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪት ማሻሻያ አዋጅ 1246/2021
- የዓለም አቀፍ ስደት ቁጥጥር በኢትዮጵያ ፡ የአለም አቀፍ የሥራ ድርጅት እና የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት፤ የአሰልጣኞች ስልጠና ሰነድ (2017)
- የጉዞ ስንቅ የሞባይል መተግበሪያ፣ በቀድሞ የሥራ እና የማህበራዊ ጉዳዮች ሚንስቴር እና ዓለም አቀፍ የሥራ ድርጅት ትብብር የተዘጋጀ (2012)

# ክፍል ሦስት

## ወደ ዐረብ ሀገሮች ለሥራ ለሚሰማሩ ዜጎች የሚያስፈልጉ የዐረብኛ ቃላቶች እና የንግግር ሀረጎች

### የሚከናወኑ ተግባራት

- *የሥልጠናውን ይዘት ማስተዋወቅ፤*
- *ተሳታፊዎች በርዕሱ ዙሪያ ካላቸው ልምድ ተሞክሮዎችን እንዲያካፍሉ ማድረግ፤*

### ከስልጠናው በኋላ ተሳታፊዎች ፡

- *በውጭ ሀገር ለሥራ የተሰማሩ ዜጎችን የሚጠቅሙ መሰረታዊ የዐረብኛ ቋንቋ ቃላቶች እና ለመግባቢያ ያክል የምንጠቀምብቸው ሀረጎች ጥቅማቸውን ያስረዳሉ፡፡*

*ዐረብኛ ቋንቋ ዓለም አቀፍ ቋንቋ ሲሆን በዋናነት በዐረብ ሀገሮች ብሔራዊ ቋንቋ ነው፡፡ ምንም እንኳ ሀገሮች የተለያየ የዐረብኛ ንግግር ዘየ ቢኖራቸውም ስታንዳርድ የሆነው የዐረብኛ ቋንቋ ግን በሁሉም የዐረብ ሀገራት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ይህን ስታንዳርድ የሆነውን ቋንቋ በውጭ ሀገር የሚሰማሩ ዜጎች ሰፊ ግዜ ሰጥተው ከሥራቸው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ቢያንስ በንግግር ደረጃ እና በቃላት ደረጃ ያሉትን እንዲለማመዷቸው ማድረግ በሥራቸው ላይ መልካም የሥራ ሁኔታዎች እንዲፈጠር ያስችላል፡፡ በመሆኑ ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን የቃላትንም ሆነ የዐረብኛ ሀረጎችን ትርጓሜ በመረዳት በንግግር ላይ እንዲጠቀሟቸው ለማድረግ በቋንቋው ባለሙያ በሆነ ሰው ዜጎችን ማሰልጠን ተገቢ ነው፡፡*

## 3.1 መሰረታዊ የዐረብኛ ቋንቋ ቃላቶች

### ቁጥሮች

| የአማርርኛው ትርጉም | የዐረብኛው አነባበብ | ዐረብኛ |
|---|---|---|
| ዜሮ | ሲፍር | صفر |
| አንድ | ዋሒድ | واحد |
| ሁለት | ኢስናን | اثنان |
| ሶስት | ሰላሳህ | ثلاثة |
| አራት | አርበዐህ | أربعة |
| አምስት | ኸምሣ | خمسة |
| ሥድሥት | ሢታ | ستة |
| ሠባት | ሠብዓ | سبعة |
| ስምንት | ሰማኒያ | ثمانية |
| ዘጠኝ | ቲሥዓ | تسعة |
| አስር | ዐሸራ | عشرة |
| አሥራአንድ | ኢሕደዐሸር | احدى عشر |
| አሥራሁለት | ኢስነዐሸር | اثنا عشر |
| አሥራሶስት | ሰላሰተዐሸር | ثلاثة عشر |
| አሥራአራት | አርበዐተአሸር | اربعة عشر |
| ሀያ | ዒሸሩን | عشرون |
| ሀያአንድ | ዋሒድወዒሸሩን | واحد و عشرون |
| ሀያሁለት | ኢስናንወዒሸሩን | اثنان و عشرون |
| ሰላሳ | ሰላሱን | ثلاثون |
| አርባ | አርበዑን | اربعون |

| | | |
|---|---|---|
| ሀምሳ | ኻምሡን | خمسون |
| ሰልሳ | ሲቱን | ستون |
| ሰባ | ሰብዑን | سبعون |
| ሰማኒያ | ሰማኑን | ثمانون |
| ዘጠና | ቲስዑን | تسعون |
| አንድ መቶ | ሚአህ | مئة |
| አንድ ሺ | አልፍ | ألف |
| ሁለት ሺ | አልፈይን | ألفين |
| አሥር ሺ | አሸረቱ አልፍ | عشرة ألف |
| መቶ ሺ | ሚአቱ አልፍ | مائة ألف |
| አንድ ሚልየን | መልዮን | مليون |
| አንድ ቢልዮን | ሚልያር | مليار |

## ቀናት እና ሳምንት

| የአማርርኛው ትርጉም | የዐረብኛው አነባበብ | ዐረብኛ |
|---|---|---|
| እሁድ | አልአሐድ | الأحد |
| ሰኞ | አልኢስነይን | الإثنين |
| ማክሰኞ | አሱላሳእ | الأثلاثاء |
| ረቡዕ | አልአርቢዓዕ | الأربعاء |
| ሀሙስ | አልኸሚስ | الخميس |
| ዐርብ | አልጁሙዓ | الجمعة |
| ቅዳሜ | አሰብት | السبت |

# ጊዜያት እና ወቅቶች

| የአማርርኛው ትርጉም | የዐረብኛው አነባበብ | ዐረብኛ |
|---|---|---|
| ጧት/ንጋት | ሱብሕ/ፈጅር | فجر (صبح) |
| የፀሐይ መውጫ | ሹሩቁሽምሥ | شروق الشّمس |
| የፀሐይ መግቢያ | ጉሩብ አሽምስ | غروب الشّمس |
| ከቀትር በፊት | ቀብልለዙህር | قبل الظهر |
| ከቀትር በኋላ | በዕደዙህር | بعد الظهر |
| ምሽት | መሳእ | مساء |
| እኩለ ለሊት | ሙንተሶፈለይል | منتصف الليل |
| ቀን | ፊነሀር | نهار |
| ዛሬ | ሀዘልየውም | هذا اليوم |
| ዛሬ ለሊት | ሀዚሂለይላህ | هذه الليلة |
| ሁልቀን | ኩልለየውም | كل اليوم |
| ሁሌ ለሊት | ኩልለለይላህ | كل الليلة |
| ትላንት ጧት | አልባሪሓ | البارحة |
| ትላንት | አምስ | أمس |
| ነገ | ገደን | غدا |
| ከነገ በኋላ | በዕደ ገድ | بعد غد |
| አንድ ቀን | ፊየውም ሚነልአያም | في يوم من الأيّام |
| ያለፈው ሳምንት | ኡስቡዕ አልማዲ | السبوع الماضي |
| ቀጣይ ሳምንት | ኡስቡዕ አልቃዲም | السبوع القادم |
| ያለፈው ወር | አሽህረልማዲ | الشهر الماضي |
| ቀጣይ ወር | አሽሽህረታሊ | الشهر التّالي |

| | | |
|---|---|---|
| ባለፈውአመት | ሰነልማዲያ | السنة الماضية |
| ቀጣይ አመት | ሰነል ቃዲማ | السنة القادمة |

# ወሮች

| የአማርርኛው ትርጉም | የዐረብኛው አነባበብ | ዐረብኛ |
|---|---|---|
| ጥር | የናይር | يناير |
| የካቲት | ፈብራይር | فبراير |
| መጋቢት | ማርስ | مارس |
| ሚያዝያ | አብሪል | أبريل |
| ግንቦት | ማዩ | مايو |
| ሰኔ | ዩንዮ | يونيو |
| ሀምሌ | ዩልዮ | يليو |
| ነሀሴ | አገስጠስ | أغسطس |
| መስከረም | ሴብቴምበር | سبتمبر |
| ጥቅምት | ኡክቶበር | اكتوبر |
| ህዳር | ኑፊምበር | نوفمبر |
| ታህሳስ | ዲሴምበር | ديسمبر |


# ቤተሰብ ውስጥ

| የአማርርኛው ትርጉም | የዐረብኛው አነባበብ | ዐረብኛ |
|---|---|---|
| ህፃን ልጅ | ጢፍል | طفل |
| ሚጠባ ልጅ | ረዺዕ | رضيع |
| ሴት ልጅ | ቢንት | بنت |
| ወንድ ልጅ | ኢብን | ابن |
| ቅድመአያቶች | አልአጅዳድ | الأجداد |
| ባል | ዘውጅ | زوج |
| አባት | ዋሊድ/አብ | (أب) و الد |
| እናት | ዋሊዳህ/ኡም | (أم)والدة |
| አጎት/በ አባት በኩል | ዐም | عم |
| አጎት/በእናት በኩል | ኻል | خال |
| አያት | ጀድ | جد |
| አክስት በእናት በኩል | ዐማ | عمة |
| አክስት በአባት በኩል | ኻላ | خالة |
| እህት | ኡኽት | أخت |
| ወንድም | አኽ | أخ |
| ወላጆች | ዋሊደይን | والدين |

# ፍራፍሬ እና የጓሮ አትክልት

| የአማርርኛው ትርጉም | የዐረብኛው አነባበብ | ዐረብኛ |
|---|---|---|
| ብርቱካን | ቡርቱቃል | برتقال |
| ወይን | ዒነብ | عنب |
| አፕል | ቱፋሕ | تفاح |
| ሙዝ | መውዝ | موز |
| የወይራ ፍሬ | ዘይቱን | زيتون |
| ሮማን | ሩማን | رمان |
| ኪያር | ኺያር | خيار |
| ሌመን | ለይሙን | ليمون |
| ማንጎ | ማንጆ | مانجو |
| መንደሪን | አፈንዲ | أفندي |
| ሀብ ሀብ | በጢኽ | بطيخ |
| ድንች | በጣጢስ | بطاطس |
| ቲማቲም | ጦማጢም | طماطم |
| ሳላድ | ኸስ | خس |
| የጎመን ዘር | ቀረንቢጥ | قرنبيط |
| ቀይ ሽንኩርት | በሶል | بصل |
| ካሮት | ጀዘር | جزر |
| ኮክ | ኾኽ | خوخ |
| እንጆሪ | ፈራውላ | فراولة |
| ጥቅል ጎመን | ከረነብ | كرنب |
| ተምር | ተምር | تمر |

| | | |
|---|---|---|
| ሚጥሚጣ | ፊልፊል | فلفل |
| ዘንባባ | ነኽል | نخل |
| ዝንጅብል | ዘንጀቢል | زنجبيل |
| አናናስ | አናናስ | أناناس |
| ጭማቂ | ዐሲር | عصير |
| የሾላ ፍሬ | ቲን | تين |
| ባቄላ | ፉል | فول |
| ዱባ | ቀረዕ | قرع |
| ሸንኮራ አገዳ | ቀሶብ | قصب |



# የቤት ውስጥ ዕቃዎች

| የአማርርኛው ትርጉም | የዐረብኛው አነባበብ | ዐረብኛ |
|---|---|---|
| መታጠቢያ ቤት | ሐምማም | حمّام |
| ሽንት ቤት | ሚርሐድ | مرحاض |
| ጣራ | ሰቅፍ | سقف |
| ግድግዳ | ጅዳር | جدار |
| ወለል | ሰጥሕ | سطح |
| በር | ባብ | باب |
| መስኮት | ናፊዛ | نافذة |
| ምሰሶ | ዑሙድ | عمود |
| ክፍል | ጉርፋ | غرفة |
| መኝታ ክፍል | ጉርፈቱ ነውም | غرفة النوم |
| ሳሎን | ጉርፈቱል ጁሉስ | غرفة الجلوس |
| ደረጃ | ደረጃ | درجة |
| ኩሽና | መጥበኽ | مطبخ |
| ቤት | (ዳር)መንዚል | منزل(دار) |
| ቤት | በይት | بيت |
| ወንበር | ኩርሲ | كرسي |
| አልጋ | ሰሪር | سرير |
| ብርድ ልብስ | በጧኒያህ | بطّانيّة |
| ፍራሽ | ፊራሽ | فراش |
| መጋረጃ | ሲታር | ستار |
| ትራስ | ዊሳዳ | وسادة |

| | | |
|---|---|---|
| ቁም ሳጥን | ዶላብ | دولاب |
| ሳጥን | ሱንዱቅ | صندوق |
| መሳቢያ | ዱርጅ | درج |
| መስታወት | ሚርአ | مرآة |
| ቁልፎች | መፋቲሕ | مفتاح |
| መቆለፊያ | ቁፍል | قفل |
| መጥረጊያ | ሚክነሳ | مكنسة |
| ማቀዝቀዣ ማሽን | ሰላጃ | ثلاجة |
| ምድጃ | ፉርን | فرن |
| በረዶ | ሰልጅ | ثلج |
| አምፖል | ሚስባሕ | مصباح |
| ሲኒ | ፊንጃን | فنجان |
| ማንኪያ | ሚልዐቃ | ملعقة |
| ሹካ | ሸውካ | شوكة |
| ሳህን | ሶህን | صحن |
| ካፖርት | ሚዕጦፍ | معطف |
| ሱፍ ኮት | በዝላ | بذلة |
| ሱሪ | በንጣሉን | بنطلون |
| ጉርድ ቀሚስ | ተኑራ | تنورة |
| ሰደሪያ | ሶደርያ | صدرية |
| የሴት ቀሚስ | ፉስታን | فستان |
| ሸሚዝ | ቀሚስ | قميص |
| ኮፍያ | ቁበዓ | قبعة |

| | | |
|---|---|---|
| ሀር | ሐሪር | حرير |
| ኮት | ሱትራ | سترة |
| ካልሲ | ጆራብ | جوراب |
| መሀረብ | ሚንዲል | منديل |
| የውስጥ ሱሪ | መላቢስ ዳኺሊያ | ملابس داخلية |
| ጓንት | ቀፉዝ | قفاز |
| ቀበቶ | ዝናር | زنار |
| ቀለበት | ኻቲም | خاتم |
| እንቁ | ሉዕ ሉዕ | لؤلؤ |
| የእጅ ጌጥ | ሲዋር | سوار |
| ልብስ | ሰውብ | ثوب |
| አልባሳት | አልመላቢስ | الملابس |
| ጫማ | ሒዛእ | حذاء |
| ማበጠሪያ | ሙሽጥ | مشط |
| ሻማ | ሸምዓ | شمعة |
| ሳሙና | ሷቡን | صابون |
| መቀስ | ሚቀስ | مقص |
| መርፌ | ኢብራ | إبرة |
| ጃንጥላ | ሸምሲያ | شمسية |
| ምላጭ | ሙስ | موس |
| ሳይክል | ደራጃ | دراجة |
| ሰዐት | ሳዓ | ساعة |
| አሻንጉሊት | ሉዕባ | لعبة |

| | | |
|---|---|---|
| ካውያ | ሚከዋ | مكوة |
| ክብሪት | ኪብሪት | كبريت |
| ተንቀሳቃሽ ስልክ | ጀዋል | جوال |
| የቤትስልክ | ሀቲፍ | هاتف |
| ካሴት | ሸሪጥ | شريط |
| ክር | ኸይጥ | خيط |
| ቢላ | ሲኪን | سكين |
| ኩባያ | ኩብ | كوب |
| ዋንጫ | ከእስ | كأس |
| ብትን ጨርቅ | ቁማሽ | قماش |



# ምግብ ቤት ውስጥ

| የአማርርኛው ትርጉም | የዐረብኛው አነባበብ | ዐረብኛ |
|---|---|---|
| ቁርስ | ፉጡር | فطور |
| ምሳ | ገዳእ | غداء |
| እራት | ዓሻእ | عشاء |
| እንቁላል | በይድ | بيض |
| ሥጋ | ለሕም | لحم |
| ቅቤ | ዙብዳህ | زبدة |
| ኬክ | ከዕክ | كعكة |
| ማር | ዐሠል | عسل |
| ጭማቂ | ዐሲር | عصير |
| ወተት | ሐሊብ | حليب |
| ሾርባ | ሐሳእ/ሾርባ | شوربة (حساء) |
| ዓሳ | ሰመክ | سمك |
| ሰላጣ | ሰልጣ | سلطة |
| የተቀቀለ ዓሣ | ሰመክ መስሉቅ | سمك مسلوق |
| የተጠበሰ ዓሣ | ሠመክ መሽዊ | سمك مشوي |
| ሩዝ | ኡሩዝ | أرز |
| ማካሮኒ/ፓስታ | መከሩና | مكرونة |
| ዶሮ | ደጃጅ | دجاج |
| እሽግ ውሀ | ሚያህመዕደኒያ | مياه معدينية |
| ወይን | ነቢዝ | نبيذ |
| ጉበት | ከብዳ | كبدة |

| | | |
|---|---|---|
| ቡና | ቀህዋ | قهوى |
| ሻይ | ሻይ | شاي |
| እንቁላል ፍርፍር | ዓጃ | عجة |
| የምግብ ዝርዝር | ቃኢመቱጦዓም | قائمة الطعام |
| አይስክሪም | ቡዛ | بوظة |
| ጨው | ሚልሕ | ملح |
| የምግብ ገበታ | ማኢዳ | مائدة |
| ፍራፍሬ | ፈዋኪህ | فواكه |

## ፎርም


| የአማርርኛው ትርጉም | የዐረብኛው አነባበብ | ዐረብኛ |
|---|---|---|
| ሥም | ኢሥመልአወል | اسم الأول |
| የአባት ሥም | ኢሥመልአብ | اسم الأب |
| የቤተሰብ ሥም | ኢሥመልዓኢለህ | اسم العائلة |
| የፓስፖርት ቁጥር | ረቅመልጀዋዝ | رقم الجواز |
| ሥራ | ወዚፈህ | وظيفة |
| ዜግነት | ጅንሲያህ | جنسية |
| የመታወቂያ ቁጥር | ረቅመልቢጣቃ | رقم البطاقة |
| የግል | ኻስ | خاص |
| የመንግስት | ሑኩሚ | حكومي |
| የካምፓኒው ሥም | ኢሥመሽሪካ | اسم الشركة |
| የፖስታቁጥር | ሱንዱቀልበሪድ | صندوق البريد |
| ፓስወርድ | ከሊመቱልሙሩር | كلمة المرور |

| | | |
|---|---|---|
| ሀገር | በለድ | بلد |
| ከተማ | መዲና | مدينة |
| የሞባይል ቁጥር | ረቅመልጀዋል | رقم الجوال |
| የስልክ ቁጥር | ረቅመልሀቲፍ | رقم الهاتف |
| ፋክስ | ፋክስ | فاكس |
| የትውልድ ቀን | ታሪኽልሚላድ | تاريخ الميلاد |
| ወር | ሸህር | شهر |
| ቀን | የውም | يوم |
| ዓመት | ሰና | سنة |
| ሙያ | ሚህና | مهنة |
| መኖሪያ ቤት | መንዚል | منزل |
| ኢሜል | በሪድኤሌክትሮኒ | بريد الإلكتروني |
| ድረገፅ | መውቂዕኤሌክትሮኒ | موقع الإلكتروني |
| ፊርማ | ተውቂዕ | توقيع |
| አቶ | ሰይድ | سيّد |
| ወይዘሮ | ሰይዳ | سيّدة |
| አድራሻ | ዑንዋን | عنوان |
| ቪዛ | ተእሺራ | تأشيرة |
| የቪዛ ቁጥር | ረቅሙተእሺራ | رقم التأشيرة |

# ምልክቶች እና ክልከላዎች

| የአማርርኛው ትርጉም | የዐረብኛው አነባበብ | ዐረብኛ |
|---|---|---|
| ክልክል | መምኑዕ | ممنوع |
| መግቢያ ነፃ | አዱኹል መጃነን | الدخول مجانا |
| ማጨስ ክልክል ነው | መምኑዕአተድኺን | ممنوع التدخين |
| መውጣት ክልክል ነው | መምኑዕአልኹሩጅ | ممنوع الخروج |
| መግባት ክልክል ነው | መምኑዕአዱኹል | ممنوع الدخول |
| መቆም ክልክል ነው | መምኑዕአልውቁፍ | ممنوع الوقوف |
| ሳብ! | ኢስሐብ | اسحب |
| ግፋ! | ኢድፈዕ | ادفع |
| ዝግ ነው | ሙግለቅ | مغلق |
| ክፍት ነው | መፍቱሕ | مفتوح |
| አደገኛ! | ኸጦር | خطر |
| ታጠፍ | ኢርጅዕ | ارجع |
| አትንካ | ላተልሚስ | لا تلمس |
| ታች | አስፈል | اسفل |
| መግቢያ | ዱኹል | دخول |
| መውጫ | ኹሩጅ | خروج |
| የሚከራይ | ሊልኢጃር | للإيجار |
| የወንድ ሽንት ቤት | ሚርሐድ ሊሪጃል | مرحاض للرجال |
| የሴት ሽንትቤት | ሚርሐድ ሊሰይዳት | مرحاض للسيدات |
| የህዝብ ሽንትቤት | ሚርሐድ ዓም | مرحاض عام |
| ቁም! | ቂፍ | قف |

| | | |
|---|---|---|
| ወደ ግራ | ኢቲጃህ የሳር | اتجاه يسار |
| ወደ ቀኝ | ኢቲጃህ የሚን | اتجاه يمين |
| የአውቶቡስ መቆሚያ | መውቂፍ አልሐፊላህ | موقف الحافلة |
| መቆሚያ | መውቂፍ | موقف |
| ዝግ | ሚቅፈል | مقفل |
| ማስጠንቀቂያ | ተሕዚር | تحذير |
| ዝግ መንገድ | ጦሪቅ መስዱድ | طريق مسدود |



# ከቦታ እና ከሰዓት ጋር የተያያዙ ቃላቶች

| የአማርርኛው ትርጉም | የዐረብኛው አነባበብ | ዐረብኛ |
|---|---|---|
| እዚህ | ሁና | هنا |
| እዚያ | ሁናከ | هناك |
| ሰሜን | ሺማል | شمال |
| ምዕራብ | ገርብ | غرب |
| ምሥራቅ | ሸርቅ | شرق |
| ደቡብ | ጀኑብ | جنوب |
| ቀኝ | የሚን | يمين |
| ግራ | የሳር | يسار |
| ውጭ | ኻሪጅ | خارجا |
| ውስጥ | ዳኺል | داخلا |
| የትም | ሐይሱ | حيث |
| ቅርብ | ቀሪብ | قريب |
| በጣም ሩቅ | አቅሷ | أقصى |
| ሩቅ | በዒድ | بعيد |
| ጎን | ጀንብ | جنب |
| በስተኋላ | ወራእ/ኸልፍ | خلف/وراء |
| በስተፊት | ቁዳም/ አማም | أمام/قدام |
| ላይ | ፈውቅ | فوق |
| ሥር | ተሕት | تحت |
| ከፍታ ላይ | ዑልያ | عليا |
| ታች | ሱፍላ | سفلى |

| | | |
|---|---|---|
| በጧት | ባኪረን | باكرا |
| በመዘግየት | ሙተአኺረን | متأخرا |
| ንጋት | ሰባሐ | صباحا |
| ምሽት | መሳእ | مساءا |
| በቅርብ | ቀሪበን | قريبا |
| ባብዛኛው | ጋሊበን | غالبا |
| አንዳንዴ | አሕያነን | أحيانا |
| በጣም ውስን | ኒዜናዲረን | نادرا |
| አሁን | አልሒን/አልአን | الأن (الحين ) |
| አካባቢ | ኺላል | خلال |
| በፊት | ቀብል | قبل |
| በኋላ | በዕድ | بعد |
| ከዛ በኋላ | በዕዴን | بعدين |
| ለሊት | ለይለን | ليلا |
| እኩለቀን | ነሀረን | نهارا |
| ከሰዐት | ዞህረን | ظهرا |
| በተመሳሳይ ጊዜ | ነፍሰልወቅት | نفس الوقت |
| ለተወሰነ ጊዜ | ሊሙዳህ | لمدة |

## መጠየቂያ ቃላቶች

| የአማርኛው ትርጉም | የዐረብኛው አነባበብ | ዐረብኛ |
|---|---|---|
| ማን | መን | من |
| መቼ | መታ | متى |
| የትኛው | አይዩ | أيّ |
| ምን | ማዛ | ماذا |
| ለምን | ሊማዛ | لماذا |
| የት | አይነ | أين |
| እንዴት | ከይፈ | كيف |
| ከ | ሚመ | مما (من + ما) |
| ስለ | ዐማ | عمّا (عن + ما) |

## መልስ መስጫ ቃላቶች

| የአማርኛው ትርጉም | የዐረብኛው አነባበብ | ዐረብኛ |
|---|---|---|
| እውነት?/እርግጠኛ? | ሳሕ/አኪድ | أكيد (صح) |
| አዎ/እሺ | አይ ነዐም/አጀል | اجل(أي نعم) |
| አይደለም | ላ | لا |
| በትክክል | ቢዶብጥ/ቢጦብዕ | بالطبع/بضبط |
| በፍፁም | አበደን | أبدا |

## 3.2 ከዐረብኛ ንግግር የሚጠቀሙ ሀረጎች

| ስለራስ መግለፅ | | |
|---|---|---|
| ስሜ (እኔ)... እባላለሁ | ኢሥሚ (አነ) | اسمي (أنا .....) |
| ከኢትዮጵያ ነው የመጣሁት | አነ ሚን ኢስዮቢያ | أنا من إثيوبيا |
| የምኖረው..... | ወአስኩኑ ፊ | وأسكن في ........... |
| እድሜየ.... | ዑምሪ | عمري ...... |
| ... እህት እና ... ወንድሞች አለኝ | ወለደየ .. ኡኽት ወ.. ኢኽዋ | ولدي ....... أخت و......... إخوة |
| በእረፍት ጊዜየ ... ማድረግ እወዳለሁ | ሂዋየቲ | هواية .......... |
| የምሰራው... ነው | አዕመሉ ፊ መጃል | أعمل في مجال ....... |
| ወደ ፊት ... ማሳካት እፈልጋለው | አርገቡ አን ኡሀቂቅ ... ፊ ሙስተቅበል | أرغب ان أحقق .......... في المستقبل. |

| ሰላምታ | | |
|---|---|---|
| እንኳን ደህና መጣህ | አህለን ወሰህለን | أهلا و سهلا؟ |
| ሰላም? | አሰላሙዓለይኩም | السّلام عليكم؟ |
| እንኳን ደህና መጣህ | መርሐበን ቢከ | مرحباً بك ؟ |
| እንዴት አደርክ? | ሰባሑልኸይር | صباح الخير؟ |
| እንዴት አመሸህ? | መሳኡልኸይር | مساء الخير؟ |
| እንዴት ነህ? | ከይፈልሐል | كيف الحال؟ |
| ጤንነት? | ከይፈሲሐቱከ | كيف صحتك؟ |
| ሰላም አደርክ? | ከይፈአስበሕት | كيف أصبحت؟ |

| መልስ | | |
|---|---|---|
| እንኳን ደህና መጣህ | አህለን ወሰህለን | أهلا و سهلا |
| ሰላም ? | ወዓለይኩምሰላም | وعليكم السلام |
| እሺ እንኳን ደህና መጣህ | መርሐባ | مرحبا |
| እንዴት አደርክ | ሰባሑልኸይር | صباح النور |
| እንዴት አመሸህ | መሳአኑር | مساء النور |
| ምንም አይል/ሰላም ነው | ዓላማዩራም | على ما يرام |
| አሪፍ (ጥሩ) ነው:: ፈጣሪ ይመስገን | ጠይብ ጀይድ አልሐምዱሊላህ | بخير و الحمدلله (جيبد / طيّب ) |

| የመሰናበቻ አገላለፆች | | |
|---|---|---|
| መልካም ቀን | ጧበ የውሙክ:የውም ሰዒድ | طاب يومك/ يوم سعيد |
| መልካም ምሽት | ጧበት ለይለቱክ/ለይላ ሰዒዳ | طابت ليلتك / ليلة سعيدة |
| ቻው/ደህና ሁን | ወዳዓን ማዐሰላማ | وداعا / مع السلامة |
| መልካም ጉዞ | ሪሕላ ሰዒዳ/ሪሕላ ሙወፈቃ | رحلة سعيدة (موفقة) |
| ቻው/ሌላ ጊዜ እንገናኛለን | ኢለሊቃእ | إلى القاء |
| በኋላ እንገናኛለን | ሰነተቃበል በዕድ | سنتقابل بعد |
| በኋላ አገኝሀለው | ሰአራከ ቀሪበን | سأراك قريباً |
| መልካም ምሽት | ተስበሕ ዓላኸይር(ኢ.መ) | تصبح على خير |

| ትህትና የተሞላበት አገላለፅ | | |
|---|---|---|
| ይቅርታ | አሲፍ | أسف |
| እባክህን/ፍቃድህ ከሆነ | በዕደ ኢዝኒክ/ለውሰመሕት /ሚንፈድሊክ | من فضلك /لو سمحت /بعد إذنك |
| ይቅርታ አርግልኝ | መዕዘረተን | معذرة |
| በጣም አመሰግናለው | ሹክረን ጀዚለን | شكرا جزيلا |
| በጣም አመሰግናለው | አልፍ ሹክር | الف شكر |

| | | |
|---|---|---|
| ችግር የለውም | ዓፍወን | عفوا |
| ደስይለኛል | ቢኩሊሱሩር | بكل سرور |
| እጅሽ ይባረክ | ሰሊምት/ሰሊመት የዱክ | سلمت/ سلمت يداك |
| ፈጣሪ ይመስገን ደህና ሰለሆንክ | አልሐምዱሊላህ ዓላሰላመቲክ | الحمد لله على سلامتك |
| መልካምህ ይብዛ | ከሱረኸይሩክ | كثر خيرك |
| ተጠንቀቅ | ኢሕዘር | احذر! |
| አመሰግናለው | ቢልሐናኢ ወሺፋእ | بالحناء و الشفاء |
| መልካም እድል | ቢተውፊቅ | بتوفيق |

| እንኳን ደስ አለህ አገላለፅ | | |
|---|---|---|
| እንኳን ደስ አለህ | መብሩክ | مبروك |
| መልካም አዲስ ዓመት | ዒድ ሚላድሰዒድ | عيد ميلاد سعيد |
| መልካም በዓል | ዒድ ሰዒድ | عيد سعيد |
| እንኳን አብሮ አደረሰን | ኩሉዓም ወአንቱም ቢኽይር | كل عام و أنتم بخير |

| ይቅርታ እና ሀዘኔታ | | |
|---|---|---|
| በጣም አዝናለው | አነ ሙተአሲፍ ጅደን | أنا متأسف جدا |
| ይቅርታ አድርግልኝ | ሳሚሕኒ | سامحني |
| አትጨነቅ | ላተቅለቅ | لا تقلق |
| ችግር የለው | ላ ሙሽኪላ | لا مشكلة |

| | | |
|---|---|---|
| ችግር የለውም | ላበእስ | لا بأس |
| እርሳው | ኢንሰልአምር | انسى الأمر |
| ይቅር ብየሀለው | ሳመሕቱክ | سامحتك |

| ስልክ ላይ | | |
|---|---|---|
| እኔ ምደውለው ከ ___ | አነ አተሲል ሚን | أنا ... أتصل من ... |
| አቶ ______ ይኖራል | ሀል ዩጀድ ሰይድ___? | هل يوجد سيّد ... |
| እየሰማሁክ ነው አውራ | ተሐደስ አስመዑክ | تحدث أسمعك |
| ሰይድ _____ የለም | አሰይድ ____ ገይር መውጁድ | السيّد ... غير موجد |
| ከ አንድ ሰዓት በኋላ ደውል | ኢተሲል በዕደ ሳዓ | اتصل بعد الساعة |
| ማን ልበል | መን አንት? | من أنت؟ |
| ምትለው ሌላ ነገር አለህ? | ሀል ለደይክ ማ ተቁል? | هل لديك ما تقول |
| የተሳሳተ ቁጥር ነው የደወልከው | ላ እተሶልተ ረቅመል ኸጦእ | لا ، اتصلت رقم خاطء |
| እንደደወልኩ ንገረው | አኽቢርሁ ቢአኒ እተሶልቱቢህ | أخبره بأني اتصلت به |
| ትንሽ ጠብቅ | ለሕዛ | لحظة ! |
| ትንሽ ጠብቅ | እንተዚር ቀሊለን | انتظر قليلا |

| | | |
|---|---|---|
| እየመጣ ነው ትንሽ ጠብቅ | ሁወ ቃዲም ለሕዛ | هو قادم لحظة! |
| ኔትወርክ በደንብ አይሰራም | አሸበካህ ገይር ሷሊሀ | الشبكة غير صالحة |
| ቆይቼ እደውላለው | ሰአተሲሉ በዕድ | سأتصل بعد |
| እቸኩላለሁ | አነ አስረዕ | أنا أسرع |
| ቻው | መዓሰላማ | مع السلامة |

| በትራንስፖርት ላይ | | |
|---|---|---|
| ሆቴሉ የት ይገኛል? | አይነ ዩጀዲል ፍንዱቅ | أين يوجد الفندق؟ |
| እባክህ መንጃ ፈቃድህን? | ሩኽሶቱል ቂያዳ ሚንፈድሊክ | رخصة القيادة من فضلك ؟ |
| ባቡር ብጠቀም ይሻላል ወይስ አውሮፕላን | ሀሊል ቂጧሩ አፍዶል | هل القطار أفضل ام الطائرة؟ |
| የአውቶቡሱ ቁጥር ስንት ነው | ማረቅሙልሐፊላ | ما رقم الحافلة؟ |
| ምን ያህል ነው ዋጋው | ከም ዩከሊፍ አዚሀብ | كم يكلف الذهاب؟ |
| ምን ያህልነው ርቀቱ | ከሚልመሳፋ | كم المسافة؟ |
| በምን ምክንያት ነው የመጣሀው? | ማሰበቡ ዚያረቱክ | ما سبب زيارتك؟ |
| በሥራ ምክንያት ነው | ዚያረቱል ዐመል | زيارة العمل |
| በጉብኝት ምክንያት | ዚያረቱል አሲያሃ | زيارة  سياحة |

| | | |
|---|---|---|
| እባክህ ፓስፖርት? | ጀዋዙሰፈር ሚንፈድሊክ | جواز السفر من فضلك؟ |
| እባክህን የመግቢያ ፎርም? | እስቲማረተዱኹል ሚንፈድሊክ | استمارة الدخول من فضلك؟ |
| ቆይታህ ምን ያህል ጊዜ ነው? | ከም ሙደቱል ኢቃማ | كم مدة الإقامة؟ |
| መልካም የቆይታ ጊዜ | ኢቃማህ ጦይባ | إقامة طيّبة |

| ሱቅ ዉስጥ | | |
|---|---|---|
| የዚህ ጫማ ዋጋ ስንት ነው? | ከም ሲዕሩ ሀዘል ሒዛእ | كم سعر هذا الحذاء |
| ሀምሳ ሪያል | ኸምሰቱ ሚአት ሪያል | خمس مائة ريا ل |
| ዋጋው ውድ ነው | ሲዕሩሁ ጋሊ | سعره غالي |
| በሌላ ቀለም አለህ? | ሀል ለደይከ ቢሎውን አኸር? | هل لديك بلون أخر؟ |
| የመልበሻ ክፍሉ የት ነው? | አይነ ሑጅረቱሉብስ | أين حجرة اللبس؟ |
| እሄን መሞከር እፈልጋለው | አወዱ አን ኡጀሪበ ሀዛ | أود أن أجرب هذا |
| እሄ ለኔ አይገጥመኝም | ሀዛ ገይር ሙናሲብ ሊ | هذا غير مناسب لي |
| ምንልታዘዝ | አዩኺድማ | أيّ خدمة؟ |
| ለማየት ነው | አነ ኡሻሂዱ ፈቀጥ | أنا أشاهد فقط |

# አስፈላጊ መረጃዎች እና ስልክ ቁጥሮች

## የኢትዮጵያ መንግስት መስሪያ ቤቶች መረጃ

| የመ/ቤቱ ስም | አድራሻ | ስልክ ቁጥር |
|---|---|---|
| የኢትዮጵያ የሥራ እና ክህሎት ሚንስቴር | ላምበረት፤ አዲስ አባባ | +251 116 671792 |
| የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚንስቴር | አዲስ አበባ<br>ፖስታ ቁ. 1037 | +251115517345<br>+251115514300 |
| የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን | አዲስ አበባ፤ ሩሲያ ጎዳና<br>ፖስታ ቁ. 199 | +251115512744<br>+251115528441 |
| የኢትዮጵያ የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት አገናኝ ኤጀንሲዎች አሰሪ ፌዴሬሽን | ቦሌ መድሃኒያለም፤<br>አዲስ አባባ | +2516634913 |

## የኢትዮጵያ በውጭ ሀገር ኤምባሲዎች መረጃ

| የሚገኙበት ሀገር | አድራሻ | ስልክ ቁጥር |
|---|---|---|
| ጆርዳን | 8B አል ቀጣን ጎዳና፤ አማን | +962798806252<br>+96265850396 |
| ሳዑዲ ዐረቢያ | አቡበከር አልካርኺ፣ ሪያድ 11693 | +966114823919 |
| የተባበሩት ዐረብ ኤምሬት | አልባጠን ጎዳና | +97126655111 |
| አማን | አሳሩጅ ጎዳና፤ መስካጥ | +96824956487<br>+96824956497 |
| ሌባኖስ | ሰይድ ፈሪሀ ጎዳና፤ ቤሩት | +9615953597<br>+9615953598 |
| ኳታር | አልካጢፍያህ ጎዳና፤ ዶሐ | +97440207000 |
| ኩዌት | ጃባሪያ ጎዳና 107፤ ኩዌት ሲቲ | +96525348198<br>+96525334291 |
| ባህሬን | ጎዳና 7319፤ ማናማ | +0097317180605 |

